# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 9 መጋቢት 4 ቀን 2014 ዓም(13-03-2022)

የዛሬውን ዘገባችንን ካለፈው ሰኞ የካቲት 28 ቀን ወዲህ ያሉትን መነሻ አድርገን የምናቀርብ ይሆናል።

በቅድሚያ ሰኞ የካቲት 28 ቀን 2014 ዓም የሸዋ ሊቃነጳጳስ የአቡነ ኤፍሬም ዜና እረፍትን ተከትሎ የተሰማንን ጥልቅ ሃዘን ለመግለጽ እንወዳለን።ለኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ አባቶችና ምእመናን ጽናትና ብርታቱን እንዲሰጣቸው ከልብ እንመኛለን።አገራችን ባለችበት በዚህ አስከፊ ወቅት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የሁለት አባቶች ማጣት ቀላል አይደለም።ሃዘኑን ድርብ ያደርገዋል።ሆኖም ግን የአባቶቻችን ጸሎትና ሱባኤ ፈጣሪ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ በረከትና ሰላም ያወርድልን ዘንድ አማላጅ እንደሚሆን አንጠራጠርም። ሌሎቹም አባቶች ከግፉአን ጎን በመቆም የፈጣሪን ትዕዛዝ ለማስፈጸም ብርታትና ድፍረቱን ይስጣቸው እንላለን።የአባታችን የቀብር ስነሥርዓት በደብረብርሃን ከተማ ተፈጽሟል።ነፍሳቸውን በአጸደ ገነት ያኑርልን!የፓትሪያርኩ የአቡነማርቆርዮስ የስንብት ስነስርዓት ቅዳሜ መጋቢት 3 ቀን 2014 በመስቀል አደባባይ የተከናወነ ሲሆን የቀብር ስነስርዓቱም በቅድስት ሥላሴ እሁድ መጋቢት 4 ቀን ተፈጽሟል።የሳቸውንም ነፍስ ፈጣሪ በአጸደ ገነት ያሳርፍልን።

በዚሁ ሰኞ እለት ብልጽግና ተብዬው የመንግሥት መንኮራኩር የማእከላዊ ኮሚቴ የሁለት ቀን ስብሰባውን የጀመረበት ቀን ነው።ይህ ስብሰባ ካለፈው ሳምንት ከተካሄደው የሥራ አስፈጻሚ ስብሰባ ቅጥያ ሲሆን ለሚከተለው የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ መንደርደሪያ ነው።በሥራአስፈጻሚው ስብሰባ የተላለፉትን ውሳኔዎች አጽድቆ ለማሳለፍ የተጠራ፣ተቀብሎ ለማድረስ ግፋ ቢል፣የፊደላት አቀማመጥን አስተካክሎ ውሳኔውን የሚያጠና እንጂ ሌላ አቋምና ውሳኔ ለማሳለፍ ወይም ለመሻር መብትም ሆነ ድፍረት የለውም።ይህ ከመቶ ስልሳ በላይ የሆኑ አባላትን ያቀፈው ማዕከላዊ ኮሚቴ ለ2000 አባላት ለሚሳተፉበት ለመጋቢቱ 2 ና4ቱ ጠቅላላ ጉባኤ መንገድ ጠራጊ ነው።የሌባና ጎሰኛ ድንኳን በሆነው ብልጽግና፣ ብልግና ቢባል ይሻላል በዬእርከኑ የሚሰዬመው ተሰብሳቢ የካድሬ ቡድን አገሪቱ ለገጠማት የኤኮኖሚ፣የፖለቲካና የማህበራዊ ቀውስ ምክንያትና ምንጭ በመሆኑ መፍትሔ ያመጣል ተብሎ አይጠበቅም።የብልጽግና መርሓ- ግብር (ፕሮግራም)የኢሕአዴግ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ቅጥያ እንደሆነ የሚያሳዩ በሕገመንግሥቱ፣በአገራዊ ባለቤትነት ላይ ያለው ብሔር ብሔረሰብ ህሳቤ እንዳለ መቀመጡ ማረጋገጫ ነው።ከዚያም በላይ ሕብረተሰቡን በዚህ አገር ጠልና ጎሰኛ ህሳቤ ለማጥመድ የተዘረጋውን እቅድ አስደንጋጭ የሚያደርገው ትውልዱን በጎሰኝነት ለመበከል ከ14 ዓመት እስከ 18 ዓመት ዕድሜ ያለውን ታዳጊ በወጣት ሊግ፣ከዚያ በላይ እስከ35 ዓመት ድረስ ያለውን ደግሞ በፓርቲ አባልነት ለመያዝ የድርጅቱ ዓላማ መሆኑ በስብሰባ ጸድቋል።የወጣቱ አይምሮ በነጻነት እንዳይጎለምስ የአንድ ሃሳብ ተሸካሚ ማድረግ በአገር ላይ ብቻ ሳይሆን በትውልድ ላይ መፍረድ ነው።ወጣቱ ትውልድ ለማመዛዘን የሚያበቃ እውቀት እንዲኖረው የአንድ ነጠላ አስተሳሰብ ባርያ መሆን አይኖርበትም ብቻም ሳይሆን በሴራ ከተተበተበ ፖለቲካ መራቅ ይኖርበታል።ዕውቀቱን አዳብሮ ለመፍትሄ የሚበቃ ትውልድ መፍጠር እንጂ የጥፋት ሃይል መመልመል መሆን አይኖርበትም።ይህንንም ማድረግ ትልቅ ወንጀል ነው።ይህንንና የመሳሰሉትን ያገር ችግሮች የችግሮቹ ፈጣሪ የሆነው ብልጽግና ይፈታቸዋል ብሎ መጠበቅ ስህተት ነው።ብልጽግና በተፈጥሮው በችግር ላይ ችግር የሚወልድ እኩይ ስብስብ እንጂ ለመፍትሔ የተፈጠረ አይደለም። የመፍትሔው ባለቤት ሕዝቡ ብቻ ነው።ለመፍትሔው መንደርደሪያም በሥልጣን ላይ ያለውን የጎሰኞች ስብስብና የዘረጋውን ስርዓት ማስገድ ነው።

በስብሰባ ላይ የሌቦቹ ግብግብና ንትርክ ፈጦ የታዩበት ሲሆን በተሰረቀው የብዙ ሚሊዮን ብር ላይም የማእከላዊ ጉባኤው አባል የሆኑት አቶ አወቀ ሃ/ማርያም የተባሉት 49.9 ሚሊዮን ብር የተሰረቀ እንጂ ብድር የሚባል ነገር እንደሌለ አረጋግጠዋል። ከዚህ አይነቱ ስብስብ ምን በጎ ነገር ይጠበቃል?

ብልጽግና ፓርቲ  የሌቦች አባላቱን መበልጸግ እንጂ የአገራችንን ብልጽግና የሚመኝና የሚፈልግ አይደለም።ባዶ ኪሱን ገብቶ የቢሊዮን ብር አንቀሳቃሽ የሚሆኑበት፣ከደሳሳ ኪራይ ቤት ወጥተው በአገር ውስጥና በውጭ አገር የብዙ ቪላና ሕንጻ ባለቤት የሚሆኑበት፣የአገራችንን መሬትና የማዕድን ሃብት እዬቸበቸቡ በውጭ አገር ባንክ የሚያከማቹበት፣የታላላቅ የንግድ ተቋማት ድርሻ (ሸር) እዬገዙ ንብረት የሚያግበሰብሱበት፣ለቤተሰቦቻቸውና ለልጆቻቸው ላሉበትና ወደፊት ለሚኖሩበት  የተቀናጣ ኑሮ የሚያመቻቹበት የሥልጣን መንኮራኩር ነው።ለዚያም ነው ይህ የማፊያ ብቻ ሳይሆን አውሬ ቡድን መወገድ ብቻ ሳይሆን በሕግ ተጠያቂ መሆን አለበት የምንለው።

በውስጡ የተነሳው የእርስ በርስ ሽኩቻ ከጥቅም አንጻር እንጂ በንጹሃንና በሌቦቹ መካከል የተደረገ ትግል አለመሆኑን ማወቅ ተገቢ ነው።ሌባ ሲሰርቅ ይስማማል፣ሲካፈል ይጣላል የሚለው አባባል ተገቢውን ትርጉም ያገኘው በብልጽግና ላይ ነው ብንል ስህተት አይሆንም። በብልጽግና ተብዬው ስብስብ ውስጥ የተነሳው የውስጥ ቀውስ ከአማራው፣ወደ ሶማሌው፣ወደ ደቡቡ፣ወደ ኦሮሞው እዬተዛመተ ድርጅቱን የሌቦች የፍልሚያ መድረክ አድርጎታል።በስርቆትና በሙስና የጨቀዬው ብልጽግና  ከጠቅላላ ጉባኤው በኋላ ምን ሆኖ እንደሚመጣ አይታወቅም።በማእከላዊው ኮሚቴው ስብሰባ ላይ እንደታዬው ከሆነ አሳሪና ታሳሪ፣አባራሪና ተባራሪ እንደሚኖር ተስተውሏል።ያም ብቻ ሳይሆን የኦሮሙማው ቡድን ሁሉንም ጠቅልሎ ለመያዝ የሚያስችለውን የጀመረውን ሥራ ሕጋዊ መልክ ሰጥቶታል ።በስብሰባው መግቢያ ላይ አብይ አህመድ በግልጽ እንደተናገረው  'እኛ የወያኔ ምልምልና ግርፍ ነን ማንም ሴረኛ ነኝ ባይ ሊሸውደን አይችልም" ሲል ሴረኞች ብሎ በመደባቸው ላይ እርምጃ ሊወስድባቸው እንደሚችል በግልጽ ተናግሯል።እነዚህ ሴረኛ ተብለው የተመደቡት ሰዎች ላለፉት 30 ዓመታት ኢትዮጵያን ለማፈራረስ፣ሕዝቡን በጎሳ ነጣጥሎ ሲያጋድልና ሲያፈናቅል ለኖረ ሥርዓት ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ሽንጣቸውን ገትረው ሲሟገቱና ሲያገለግሉ፣በንጹሃን ህይወት መጥፋት፣በማሰቃዬትና በማፈናቀል ሚና የተጫወቱ መሆናቸውን ሕዝቡ ያውቀዋል። ሌባ ሌብነቱ ሲጋለጥ፣የሥልጣን ዘመኑ ሲያከትም፣ ተገልብጦ የሕዝቡን ብሶት በመንጠቅ የአዞ እምባውን ቢረጭ ከወንጀል ተጠያቂነቱ ነጻ ሊሆን አይገባውም።እራሱን ወቅሶ ይቅርታ ቢጠይቅ እንኳን ይቅርታ ከጠየቀበት ጊዜ በፊት ለፈጸመው ወንጀል ሊጠዬቅ ይገባዋል።ያ ሳይሆን  ወንጀለኛውን ጉዳተኛና የሕዝብ ወገን አድርጎ መቁጠር የፍትሕን ዋጋና ትርጉም ማሳጣት ይሆናል።

የኢሕአዴግም ሆነ የብልጽግና  ሌቦች በውጭ አገር ያከማቹትን ሃብት ለማስመለስ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንቅስቃሴ ማድረግ ይገባል።በውጭ አገር የሚኖሩ የሕግ ባለሙያ ኢትዮጵያውያን በዚህ ዘመቻ ላይ የመሰለፍ አደራቸውን እንዲወጡ ጥሪ እናደርጋለን።እርግጥ ነው የዓለም አቀፉ የዘረፋ መረብ በቀላሉ የሚሸነፍ ወይም የሚበጣጠስ አይሆንም።የአገሩንና የሕዝቡን  መብት የሚያከብርና የሚያስከብር ፍጹም አገር ወዳድ የሆነ መንግሥት መኖር ወሳኝ ነው።ያም አይነቱ መንግሥት የሕዝቡ ድጋፍ ስለሚኖረው ጠንካራና የማይደፈር፣የጠየቀውን  የሚያገኝ ይሆናል።አገራችንን የውስጥና  የውጭ አገር መጫወቻ ያደረጋት  ጠንካራ ሕዝባዊ መንግሥት አለመኖር ነው።ላለፉት 30 ዓመታት በሥልጣን ላይ ያለው ጎሰኛ ከሃዲ አገር ጠል ቡድን ይባስ ብሎም የአገርን ቋሚ ሃብትና ንብረት የሚያሸሽና  ለባዕዳን በሽያጭና ሽርክና ስም አሳልፎ የሚሰጥ አቀባባይ ቡድን  በመሆኑ ይበልጥ የተረፉትንም ይቸበችባል እንጂ  የወጡ ንብረቶችን ያስመልሳል ተብሎ አይጠበቅበትም። በብልጽግና በኩል የቀረበው መርሃ-ግብር ከወያኔ ያልተለዩ፣መሆኑን ባለፈው ሳምንት ዝግጅታችን ላይ ገልጸነዋል።አዲስ አበባን የመዋጡና

ፊንፊኔ ብሎ የመሰዬሙ፣የመሬት ባለቤትነትና በአጠቃላይ የስርዓቱ አወቃቀርና ሕገመንግሥቱ ጭምር እንዳለ የሚቀጥል መሆኑ በሥራአስፈጻሚው፣በማእከላዊ ኮሚቴው ስብሰባ ተረጋግጧል።የጠቅላላ ጉባኤውም ውሳኔ ተመሳሳይ ነው። ዝርዝሩን ወደ መጨረሻው ላይ እናቀርባለን።

ወደሌሎቹ የሰሞነኛዎቹ አበይት ጉዳዮች ዝርዝር ስናመራ

ከአለፈው ሳምንት ጀምሮ በመካሄድ ላይ ያለው የአማራ ፋኖና የልዩ ሃይልን የማዳከም ብሎም የማጥፋት ዘመቻ ተጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን በተለይም በጎጃም ቡሬና በደቡብና ሰሜን ወሎ መንግሥት ነኝ ባዩ የክልሉ አስተዳደር በመለመላቸው ጥቂት ሆድ አደሮች ያደረገውን ከበባ ነዋሪው ሕዝብ ነቅሎ በመውጣት ለፋኖና ልዩ ሃይሉ ያለውን ድጋፍና አንድነቱን በማሳዬቱ፤ሊከብና ሊያፍን የመጣው ተላላኪ ጦር ያሰበውን ሳያደርግ ሊመለስ ችሏል።ከቀናት በኋላ ግን ተመልሶ ከፋኖ ጋር በተደረገ ግጭት ከሁለቱም በኩል የአምስት ሰዎች ሕይወት ጠፍቷል። አሁንም የኦነጉ ብልጽግና ከወያኔ ጋር ተባብሮ ፋኖንና የአማራ ልዩ ሃይልን ለማጥፋት ተጠናክሮ በመንቀሳቀስ ላይ ነው።እነዚህ ሕዝባዊ ሃይሎች ካሉ የወያኔና ኦነግ መራሹ ብልጽግና ስምምነት ሊሳካ አይችልም።የአማራውን መሬት የወልቃይትንና ጠገዴ፣ ራያና አዘቦን በቀላሉ ለማስረከብና ለመረከብ ያዳግታል።

ከወያኔ እንቅስቃሴ ሳንወጣ ከሱዳን ወደ መቀሌ ሽሬ ተደጋጋሚ በረራ ያደረገው የአንቶኖቭ አይሮፕላን ምስጢር አነጋጋሪ ሆኗል።በመከላከያ አባላቱ ጥያቄ ያስነሳው ይህ በረራ በሰሜኑ ጦር አመራር በኩል ልዩነት ፈጥሯል። በአንድ በኩል ለምን እርምጃ አይወሰድም ሲባል በሌላው በኩል በተለይም በአዛዡ በኦነጉ ጀነራል ጌታቸው ጉዴና በኩል “ምን አገባችሁ፣ከላይ የተወሰደ የፖለቲካ ውሳኔ ነው” በማለት ሌሎቹን ለማሸማቀቅ ሞክሯል።ዝርዝሩ ባይታወቅም በረራው ወያኔ በመሬት ያጣውን በር በሰማይ አስከፍቶ የጦር መሣሪያና የሌላም እርዳታ ለማስገባት የተሰጠው ዕድል መሆኑ ብዙዎቹ ያምኑበታል፤የእኛም እምነት ከዚያ የተለዬ አይደለም።ይህም ብቻ ሳይሆን በሱዳንና ኢትዮጵያ የመተማና ገላባት ድንበር የመከፈቱ እርምጃ ለወያኔና ለሌሎቹ አማጽያን ነጻ እንቅስቃሴ የተደረገ ድጋፍ እንጂ ሰላም በመስፈኑ የተወሰደ እርምጃ አይደለም።የዚህ ጥምር ውጤት ለተጠናከረ አገር የመበታተንና የሕዝብ እልቂት በር የሚከፍት ነው ።ያንን ተከትሎ ከቤንሻንጉልም የልዩ ሃይሉ መተከልን ለቆ እንዲወጣ መደረጉ በከባቢው አማጽያን በኩል ለሰላምና ለእርቅ ያቀረቡትን ጥያቄ ተከትሎ ነው ቢባልም የጉምዝና ወያኔ ኦነግና ሌሎቹ አሸባሪዎች ይበልጥ እንዲጠናከሩና እንዲስፋፉ ዕድል የሚሰጥ ለመሆኑ ከውሳኔው ማግስት ከሙቶ በላይ የግድቡ ሰራተኞችና ሾፌሮች እንዲሁም የመከላከያ አባላት መገደላቸው የሴራው ሰንሰለት መርዘሙንና መጠናከሩን ያሳያል።ነገ የግድቡ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችልም አመላካች ነው።

የሰሞኑ ሌላው ትእይንት የአዳነች አበቤ”እሽ አትበሉኝ የሹም ዶሮ ነኝ” በሚል ትእቢት በአድዋ ድል በዓል አከባበር ላይ ተሳትፎ አድርገው ያደመቁትን የአዲስ አበባ ወጣቶች የማደን ዘመቻ ነው። ከንቲባዋና ሌሎቹ የመንግሥት ባለሥልጣናት በወጣቶቹ ተሰድበናል በሚል ውንጀላ ሥልጣናቸውን በመጠቀም በሰላማውያን ላይ የሚፈልጉትን እርምጃ ወስደዋል።ከድብደባ እስከማሰር በሚደርሰው እርምጃ ብዙ ወጣቶች ተጎድተዋል።በአድዋ ድል በዓል ላይ ብቻም ሳይሆን በማግሥቱ በሚከበረው መንግሥታዊ ትኩረት ባልተሰጠው፣ተገንጣዮች በሚያንኳስሱት የካራማራ የድል በዓል መታሰቢያ ቀን በሰላማዊ መንገድ ባከበሩት የከተማዋ ነዋሪዎች በተለይም በባልደራስ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ላይ ተመሳሳይ እርምጃ ተወስዶ ከሰላሳ በላይ በፖሊስ ተወስደው ከታሰሩ በኋላ ፍርድ ቤት ቀርበው የቀጠሮ ቀን ተቆርጦባቸው ወደ እስር ቤት ተመልሰዋል።አሁንም ድረስ ወጣቱን የማደኑ ተግባር በስፋት ቀጥሏል።ከሁለት ወራት በፊትም ሰድቦናል በሚል ክስ ያጋለጣቸውን ጋዜጠኛ ታምራት ነገራን አሥረው እስከ አሁን ድረስ ክስ ሳይመሰረትበት በኦሮሚያ ፖሊስ ጣቢያ እዬታሸ ይገኛል።ሃሳብና

ትችትን እንደ ጦር የሚፈራው ተረኛ ቡድን ሳናጣራ አናስርም ያለውን የራሱን ቃል ውጦ ግፍ እዬፈጸመ ነው።ወያኔስ ከዚህ የተለዬ ምን ሠራ? ልዩነቱ በትግሬና በኦሮሞ ፋሽስቶች በየተራ መፈጸሙ ብቻ ነው።ሕዝብን ያላከበረ መንግሥትም ሆነ ቡድን ከሕዝቡ ከበሬታን መጠበቅ አይኖርበትም። የሥራውን ያገኛል!በጣም የሚያሳዝነውና የሚያስተዛዝበው ግን አንዳንድ ምሑራን ተብዬዎች ባለሥልጣኖች መሰደብ የለባቸውም፣በሰደበ ላይ እርምጃ ቢወሰድ ተገቢ ነው ማለታቸው ነው። በሚሳደብ ባለሥልጣን ላይ ግን እርምጃ ይወሰድበት ሲሉ አይሰማም።ለምሳሌም የአዲስ አበባን ሕዝብ የኮንዶም ትራፊ፣ፈርሳምና ከርሳም ያሉት የኦሕዴድ ብልጽግና አነጋውያን ሹመኞች ባወረዱት ነውረኛ ስድብ ሲሾሙና ሲሸለሙ እያዩ ዝምታን መርጠዋል።የአዲስ አበቤ ደሃ ልጅ ግን ይገረፍ ሲሉ ፍርደ ገምድል ሆነዋል። ሕዝብ ሲመረው መሪዎቹን በአግቦና በቅኔ መተረቡ የተለመደ ነው።ብልህ መሪዎችም በተባሉት ሳይበሳጩና በተራቢው ላይ ጥቃት ሳይሰነዝሩ የተባሉበትን ምክንያት መርምረው ለመታረም የሚጠቀሙበት መካሪ አድርገው ይቆጥሩታል። የኦነጋውያን ግን ከዚህ የተለዬ ነው። ሌባ እናት ልጇን አታምንም እንደሚባለው ኮሽ ባለ ቁጥር ይደነብራሉ፤ሲደነብሩም የሚያደርሱት ጥፋት መጠን አይኖረውም።በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ ይሆናል።

የኦሮሙማው ኦሕዴድ መራሹ ኦነግ ቡድን የጥፋት ዘመቻ የከፈተው በግለሰቦችና በተቃዋሚዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በተቋማትም ላይ ነው። ከከፈተባቸው አገራዊ ተቋማት አንዱ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ተቋም ነው።የኦሮሙማው ቡድን ሁሉንም ዘርፍ በመዳፉ አስገብቶ ለመቆጣጠር ካለው ስግብግብ ዓላማ ለ81 ዓመት አገልግሎት ሲሰጥ በቆዬው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ሠራተኞች ላይ የወሰደው እርምጃ አንዱ ማሳያ ሆኗል።ለዓመታት ባላቸው እውቀት ሲያገለግሉ የነበሩትን ባለውለታ ጋዜጠኞች ለሥራቸው ተመጣጣኝ ክብርና ምስጋና ተችሯቸው የጡረታ መብታቸው ተከብሮላቸው ማረፍ ሲገባቸው ካለምንም ዋስትናና ምስጋና ሁለት ቋንቋ አትችሉም በሚል ፈሊጥ ከሥራ ገበታቸው ላይ ማባረር መንግሥት ካለው የተረኝነትና የቋንቋ ምርጫ የተነሳ የጠባቦች እርምጃ ለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም።ሕገወጥ እርምጃ ስለሆነም ሊወገዝ ይገባል።የነጻ ሚዲያና የጋዜጠኞች መብት ደጋፊ የሆነ ሁሉ ከጋዜጠኞቹ ጋር ሊቆም ይገባል።የአንዱ መጠቃት የሁሉም መጠቃት ነው።ይህ ከኢዜማ አባልነት የሁለት ቋንቋ መስፈርት የተቀዳ ውሳኔ በተለይም ነጠላ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነውን የአማራ ተወላጅ ነጥሎ ለመምታት የታሰበ በመሆኑ ከአጠቃላዩ አማራን ነጥሎ ከማጥቃቱ ዘመቻ ተለይቶ አይታይም። ሁለገብ ዘመቻ የተከፈተበት የአማራው ተወላጅ ከሚሰነዘሩበት ጥቃቶች ሁሉ ለመዳን የግድ መደራጀትና መከላከል ፣አንድነቱን ለመቦርቦር የሚሸረብበትን ተንኮል አውቆ እጅ ለእጅ ተያይዞ በመቆም ደባውን ማክሰም ይኖርበታል።

በተመሳሳዩም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ጠባብ የኦሮሞ ተወላጆች በቀሰቀሱት ፊንፊኔ ኬኛ ረብሻ ትምህርት ከመስተጓጎሉ በላይ ውጥረት እንዲሰፍን ሆኗል።ያ ከኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነትና የዴሞክራሲ መብት ትግል አልፎ ለአፍሪካና ለሌሎች አገር ሕዝብ ነጻነት ድምጹን ያሰማበት ተማሪ የዋለበት መስክ የጠባቦች መፈንጫና ማላገጫ፣ የኦሮሙማ ጭፍን ጥላቻ ማስተናገጃ ሆኖ ማዬት ያገራችን የትምህርት ደረጃ መንኮታኮት ያመጣው የአይምሮ መቅጨጭ ነው እንላለን።ይሻሻላል ብለን እንዳንጠብቅም የትምህርት ሚኒስትር ሆኖ የተሾመው የዚያው የጠባቦች አጋር የሆነው የግንቦት ሰባቱ የአሁኑ ኢዜማ ሊቀመንበር የሆነው ብርሃኑ ነጋ ነው።እሱ በሚመራው የትምህርት ተቋም የኦሮሞ ጠባቦች ያሰናዱት የአገር ጠል የትምህርት መመሪያና መጽሃፍ ፣በስዕልና በመዝሙር የሚስተጋባው የፈጠራ ትርክት ወጣቱን ሲበክለው እያዬና እዬሰማ ዝም ከማለት በስተቀር ሥልጣኑንና ሃላፊነቱን በመጠቀም እርማት እንዲደረግ አላደረገም። የትምህርት ሚንስትር ተቋም የትውልዱ የእውቀት ደረጃ ተመሳሳይነት እንዲኖረውና ለአገራዊ የትምህርት መመሪያ መሻሻል ብሎም የዓለም አቀፍ ዘመናዊ

እውቀትን የሚጋሩበት መሆን ሲገባው ለመንደርተኛ ትርክት ማስፋፊያ መሆኑ ያሳዝናል።ጠባቦቹ ጭንቅላታቸውን ብቻ ሳይሆን አገራቸውን ኢትዮጵያንም ለማጥበብ ተግተው እዬሠሩ ነው።

ሌላው የሰሞኑ ጉዳይ ሁሉንም ዜጋ አስጨንቆ የያዘው የኑሮ ውድነት ነው።ከሁለት ሳምንት ወዲህ በተጀመረው በኡክሬኑና በሩስያ ጦርነት ምክንያት ተባባሰ የሚል ወሬ ቢናፈስም የሕዝቡ ኑሮ ከድጡ ወደማጡ መሆን ከጀመረ ዓመታት አልፈዋል።የአገርን ዕድገትና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ በሕንጻና በመናፈሻ የሚመትረው መንግሥት ከመጣበት ከአራት ዓመቱ ወዲህ ያለውን ብንመለከት ለወሬ ማማሟቂያ ይህን ያህል ፐርሰንት አደገ ቢባልም፣ የሕዝቡ ኑሮ ያው በገሌ ነው። የዕድገቱ መለኪያ የሆነው በባለሥልጣናቱና በቤተሰባቸው ያለው የቅንጦትና አስረሽ ምችው ኑሮ ነው።የእለት ጉርስና ቀላል ሕክምና በተነፈገው ሕዝብ ኪሳራ ለእረፍትና ለአነስተኛ ሕመም ሕክምና በሚል ሰበብ ውጭ አገር መሄዱ፣በእግሩ ለሚኳትነው ሕዝብ በቂ መጓጓዣ ሳይኖረው ፣በመኪና ላይ ቅንጡና ውድ መኪና ገዝቶ ማሽከርከሩ፣የአገር ውስጥ ጨርቅ ለመልበስ ሳይታደል እርቃኑን የሚሄደው ደሃ ሕዝብ ይታዘበናል ሳይሉ ከውጭ አገር ውድ አልባሳትና ጌጣጌጦች ማግበስበሱ የእድገቱ ማሳያ ተደርጎ ተወስዷል።ባለሥልጣኖቹ በውጭ አገር ምግብና መጠጥ ሲንደላቀቁ ደሃው በአገር ውስጥ ምርት የመጠቀም አቅም ተነፍጎታል። ከውጭ አገር ነዳጅ ጋር ያልተቆራኘው በአገር ውስጥ መመረት ያለበት የምግብ የዋጋ ንረቱ ጆሮ አይሰማ ያሰኛል።በየቀኑ ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አይታይም።እንኳንስ ዘንቦብሽ እንደውም ጭቃ ነሽ እንዲሉ የሕዝቡ ኑሮ ከድጡ ወደማጡ ተዘፍቋል።የዕድገቱ ማሳያ የሆነው የዋጋ ጭማሪው ሳይሆን አይቀርም።በአገር ውስጥ መመረት የሚገባው የምግብ ዘይትና ስንዴ በበረዶ ከተዋጠ አገር ገዝቶ ማምጣቱ ድክመትን እንጂ እድገትን አያሳይም። የቅባት እህሎች ማለትም ሱፍ፣ ኑግ፣ተልባ፣ሰሊጥ---ወዘተ በሚመረቱበት አገር የዘይት ያለህ ብሎ መጮህ፣ ቲማቲምን ከኬንያ ሸንኩርትን ከሱዳን የማስገባቱም ምክንያት የንግድ ልውውጡን ሚዛን ለማስጠበቅ ነው ሊባል ቢቻልም እንኳን፣የዋጋ ንረቱ ግን የሚያሳዬው እጥረት መኖሩን ነው።ኢትዮጵያ የራሷን ሽንኩርትና ቲማቲም አምርታም ወደ ሌላው አገር ከመላክ የሚያግዳት አቅመቢስ አገር አይደለችም።ሌላውም አገር ቢሆን የራሱን አሳድጎ፣ከሌላው አገር በርካሽ ያገኘውን ምርት መልኩንና ስሙን ወይም አዘገጃጀቱን ቀይሮ ለሌላው አገር ይሸጣል።ለምሳሌም ቲማቲሙን የታሸገ ሳልሳ በማድረግ ማለት ነው። ኢትዮጵያን የሚያክል ትልቅና ምቹ ፣የለም አፈርና ከበቂ በላይ ውሃ ባለቤት፣ በአንድ ወቅት የዳቦ ቅርጫት ተብላ የተጠራች አገር የልመና ኮረጆ ተሸካሚ ተብላ ስትጠራ መስማትን የበለጠ የሚያሳፍር ነገር የለም። ከኪሎሜትር በላይ ቆፍረው በሚያገኙት መጠነኛ ውሃ ከሚያመርቱት ከአረብ በረሃማ አገሮች ለምኖ ሕዝብን ከመመገብ ያህል ውርደት የለም።ለአረቦችም ሆነ ለሌላው አገር በብዛት የምናቀርበው ቢኖር አምራች ሃይሉን ወጣቱን ስደተኛ፣አሽከርና ገረድ በማድረግ ትውልዱን መስዋእት ማድረግ ነው።ያ ደግሞ ህሊና ላለው ዜጋ በጣሙን ያማል።

ከሰነፍ ገበሬ ደጃፍ ብልጥ ገበሬ ሞፈር ይቆርጣል እንዲሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ደሃው ዜጋ ተነፍጎት ደቾች ሰፊ አቮካዶ የሚያመርቱበት ለም መሬት ይዘው ዘይት እዬጨመቁና በፍራፍሬ መልክ ለአውሮፓ ገበያ በውድ ዋጋ ሲያቀርቡ የጥቅም ተካፋይ የሆነው መንግሥት ቅድሚያ ለአገር ውስጥ ገበያ ይሁን አላለም።እንደ አበባው ምርት የሸያጩ ገንዘብ እንደወጣ የሚቀር የዘራፊዎች ሲሳይ ሆኗል። ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ የኑግ አምራች አገር ፣የሌሎቹም የቅባት እህሎች ባለቤት እንደመሆኗ መጠን ለአገር የሚያስብ መንግሥትና ስርዓት ቢኖር የዘይት ችግር ባልተከሰተም ነበር።፣ከራሳችን አልፈን ለሌላው በተረፍን ነበር።

በዘይቱ ዙሪያ የመንግሥት የእርስ በርሱ የሚቃረነው መግለጫው ደግሞ የንግድ ሚኒስትሩ

ከ40 ሚሊዮን ሊትር በላይ ዘይት አገር ውስጥ ለማስገባት ተገዝቶ  መንገድ ላይ ነው ሲል የገንዘብ ሚኒስትሩ እንደዚያ ያለውል ያልተፈጸመና ውሸት ነው ሲል አጋልጧል።

ዘይት አጣሁ ብሎ የሚጮኸው ሕዝብ ሙብቱን ሲገፉት፣ሲገደል፣ሲፈናቀል፣ልጆቹ ሲታሠሩ ድምጹን ለማሰማት አልደፈረም።ከሰብአዊ ክብሩና ከህይወቱ ይልቅ ሆዱን ያስቀደመ ይመስላል።"ሆዱን የወደደ ማዕረጉን ይጠላል" ነውና የጨካኞቹ አገዛዝ በድክመቱ እዬገቡ ፣በችግር ላይ ችግር እዬደራረቡ ያሻቸውን ከማድረግ አልተቆጠቡም። እርግጥ ነው የሰው ልጅ ለመኖር ሙብላት አለበት፤ግን ለሙብላት ብቻ መኖር የለበትም።ለሙብላትም የመኖር ሙብትን ማስከበር፣ሙብትንም ለማስከበር መታገልን ይጠይቃል። የግፍና የመከራ ቋት ተሸካሚ የሆነው ሕዝብ ከጎረቤቱ የሱዳን ሕዝብ ሊማር ይገባዋል። ሱዳኖች ሱካር በመወደዱ ብሎም በመጥፋቱ የተነሳ ሁለት መንግሥታት ከሥልጣን አባረዋል።ምንም እንኳን ተተኪዎቹ ወታደራዊ መንግሥት ቢሆኑም ለጊዜው የነበረውን የሱካር ጥያቄ ለመመለስ ሞክረዋል።ያሁኑም የሱዳኖች የዳቦ ጥያቄ መንግሥትን ወጥሮ ይዞታል፤በውስጣው  ቀውስ እዬተናጠ ነው።ለመውደቁም ምክንያት ሳይሆን እንደማይቀር አቅጣጫው ያመለክታል።

የኦሕዴድ ኦነግ መራሹ ብልጽግና የሕዝብና የአገር ጉዳይ ቅደም ተከተል ተምታቶበት በራሱ ዓለም የሚባዝን ሆኗል። እቅዱ ቅደም ተከተሉን ካልጠበቀ የአገር ቀርቶ የቤተሰብ ኑሮ አይለወጥም።የአገራችን የኤኮኖሚው ዋልታና ማገር የገጠሩ የእርሻ ሙያ መሆኑ የማይታበል ሃቅ ነው።ከ80% በላይ የሕዝቡ መተዳደሪያ መሬትና ከመሬት ጋር የተያያዘው የእርሻ እንቅስቃሴ ነው።ይህንን መስክ( ሴክተር) የማዘመንና የማሳደግ ሥራ ቅድሚያ ካልተሰጠው ሕዝብ የሚመገበውን ካላገኘ ሌላው እድገት አይታሰብም።ለከተማዎች ማደግና መሻሻልም የጀርባ አጥንቱ ገጠሩ ነው።ገጠሩ ካልተሻሻለ ከተማ አይሻሻልም፤እንደውም  የሕዝቡ ስደት ወደ ከተማ ይሆንና የሥራ አጡ ቁጥር እዬጨመረ የብዙ ችግሮች መከሰት ምክንያት ይሆናል። ወንጀል፣ሽርሙጥና፣ሌብነት፣ዘረፋ፣ የበሽታ መስፋፋት ከድህነት ጋር የሚመጣ የማህበረሰብ ችግር ነው።

በከተማዎች የሚካሄደው የድንጋይ ቁልል (ሕንፃ)ከሕዝቡ አቅምና ከፍላጎቱ ጋር የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል።የከተማ ማሳመሩ ውድድር ከድህነት ተላቀው ከደላቸው አገሮች ከተማዎች ጋር ሳይሆን ትግሉ ለዘመናት ከተንሰራፋው ድህነት ጋር  መሆን አለበት። በጨፈቃና በስንጥር ገረገራ፣ከእንስሳት ጋር ተዳብሎ የሚኖረውን ሕዝብ በንጹህ ጎጆ  እንዲኖር ማድረጉ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል።ከቁሻሻ ወራጅ ወንዝ ከእንስሳት ጋር ተጋርቶ የሚጠጣውን የሰው ልጅ ንጹህ ውሃ እንዲያገኝ ማድረጉ አንዱና ዋናው የመንግሥት ተግባር ነው። የአሁኑ ትውልድ በአኗኗሩ፣በአመጋገቡና  በአለባበሱ እንዲሁም በአስተሳሰቡ ካለፈው ሙቶ ና ከዚያም በፊት ከኖረው ደሃ የተለዬ መሆን ይኖርበታል።አመጋገቡም ሆነ አለባበሱ ስረመሰረቱን ባይለቅም አዘገጃጀቱ የተለዬ ቢሆን ይመረጣል።የዕድገትም መለኪያው የዛሬው የሕዝቡ ኑሮ ከትናንትናው ተለውጦ ሲገኝ  ነው።በአገር ምርት መጠቀም፣ ማጌጥና መዋብ አንዱ እራስን በራስ የመቻል ማሳያ መንገድ ነው።አላስፈላጊ የውጭ ምንዛሬ ጥገኝነትንም ያሰግዳል።የሰው ጌጥ አያደምቅ ነውና በሌሎች አገሮች ምርት መመካትና  ጥገኛ መሆን ለተደጋጋሚ ቀውስ ዳርጎናል። የ66ቱ የነዳጅ እጥረት ከአሁኑ የኡክሬንና የሩስያ ጦርነት ካመጣው የነዳጅ ቀውስ ጋር ያመጣብንን ማጤኑና መፍትሔ መፈለጉ ነገ የማይባል ተግባር ነው።ብልህ ሰው ደጋግሞ ጉድጓድ ውስጥ አይወድቅም።

ከሃምሳ ዓመት በፊት እንዳለ የተነገረለት የኦጋዴው የጋዝና ነዳጅ ጉዳይ ምን ላይ እንደደረሰ ለሕዝቡ ግልጽ አይደለም ።እዬወጣ ይሸጣልም የሚል ጭምጭምታ ይሰማል።በቅርቡም በወሎ ክ/ሃገር በወረኢሉና ካቤ አካባቢ ተገኘ የተባለው የነዳጅ ዘይት በመንግሥት በኩል ትኩረት ያልተሰጠው ለምን እንደሆነ ለሕዝቡ ሙብራራት ይኖርበታል።ከኗላችን ሱዳኖች አውጥተው ሲጠቀሙ ኢትዮጵያውያንን

ተብትቦ ያሰረን ገመድ ምን እንደሆነ ማወቅ ይኖርብናል፤እቅጩ ይነገረንና እንወቀው። ከሌለም ተስፋ ቆርጠን እንቀመጥ ወይም እያለ ላለመጠቀም ያስገደደን ችግር ካለ እንወቀውና ችግሩን አሶግደን ለመጠቀም የምንችልበትን መንገድ ቀይሰን እንንቀሳቀስ።ከሁሉም በፊት ግን ያገራችንን አንድነትና የሕዝቡን የበላይነት ለማረጋገጥ እንቅፋት የሆነውን የጎሳ ፖለቲካና መመሪያ፣ከነአስተሳሰቡ ማሶገድ አስፈላጊ ነው።ኢትዮጵያ ጠሉ የጎሰኞቹ ሥርዓት እስካለ ድረስ የተፈጥሮ ሃብት፣ መሬትና ማዕድን ይበልጥ የሚፋጁበት እንጂ በጋራ የሚጠቀሙበት አይሆንም።አሁን በስፋት የሚታዬው የኦሮሙማው አፍቅሮ ከባቢ የሆነው የልማት እንቅስቃሴ የዚያ ማሳያና መንደርደሪያ ነው።

በአገራችን የሚከናወነው የልማት እንቅስቃሴ ለአንድ ለተወሰነ ከባቢ ጥቅም ብቻ የሚያተኩር ሳይሆን ዕድሉ ለሁሉም የሚዳረስ መሆን ይኖርበታል።ባለተረኞች ለመጡበት ከባቢ ብቻ የሚያስቡ ከሆነ አገራዊ ስሜቱ ይዳከማል፤የአንድነት ሰንሰለቱንም ይበጣጥሰዋል።በቦታው የሚያቆጠቁጠው ጠባብ መንደርተኝነት ይሆናል።ባገራችንም ላለፉት ሰላሳ ዓመታት የሰፈነው ይኸው አሠራር ነው።ይህ አይነቱ ድርጊት ሊወገድ ይገባል።የሚወገደውም የሁሉም፣ለሁሉም፣በሁሉም የሆነ ሥርዓት ሲሰፍን ብቻ ነው።

ሃፍረተቢሱ የኦሮሙማው ስብስብ በዜና ክፍሉ በኩል ለቀጣዩ ብሔራዊ ውይይት የገዳ ሥርዓት ያገሪቱ የፖለቲካ መስመርና መመሪያ እንዲሆን፣የወሎ ክ/ሃገርም የኦሮሞ አካል መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ ይዞ ለመቅረብ መወሰኑን አስታውቋል። ሁሉ ኬኛ የሚለው የእብደትና የጅቦች ጩኸት የሚያሰማው የጠባቦች ቡድን በብልጽግና ስም ቢመጣ ከነበረውና ከተሸከመው የጎሳ ማንነት የተለዬ ለዘመናዊ አስተሳሰብ፣ለጋራ አገር ግንባታ ፣ለሕዝብ ጥቅምና ዘላቂ ሰላም የሚረዳ ሃሳብ ያቀርባል ተብሎ አይጠበቅም።

ከሰሞኑም በአዲስ አበባ ከተማ የኦሮሚያ መንግሥት ፕሬዚዴንት ጽ/ቤት መገንቢያ ይሆናል በሚል ምክንያት ፍላሚንጎ በተባለው አካባቢ ለብዙ ዓመታት የኖሩ ዜጎች ካለምንም ካሳና ምትክ በሦስት ቀናት ውስጥ ቤታቸውን ለቀው እንዲወጡ ተወስኖባቸዋል።በስማቸው ባልከፈቱትና በማያውቁት የባንክ ቁጥር ገንዘብ ገብቶላችኋል ቢባሉም እንደማያውቁና እንዳልደረሳቸው ኑዋሪዎቹ ገልጸዋል። እንዲህ አይነቱ የተረኝነት ግፍና በደል እስከመቼ የሚለው መልስ ያላገኘ ጥያቄ ነው።አዲስ አበባ የሁሉም ሕዝብ መኖሪያና መናገሻ እስከሆነች ድረስ ለአንድ ጎሳ የምትሰጥ አይደለችም። ቀደም ሲልም የኦሮሞ ፍርድ ቤት፣የኦሮሞ መጽሃፍትቤትና ሙዚዬም --ወዘተ የሚሉ ሕንጻዎች በሕዝብ ገንዘብ ለመገንባት ተወስኖ ሥራዎቹ በመጣደፍ ላይ ናቸው።በዝምታ የታለፈው ተረኛ ቡድን በቃህ ካልተባለ ያሰበውን ኢትዮጵያን አፍርሶ ኦሮሚያ የተባለ በታሪክ የማይታወቅ አገር የመመሥረት ዓላማውን ከግቡ ማድረሱ እንደማይቀር አካሄዱ አመላካች ነው።ምንም እንኳን የክልል ሥርዓትና የጎሰኞች ፖለቲካ ይወገድ የሚል አቋማችን ቢሆንም የክልል ስርዓት እስካለ ድረስ በከተማዋ የሁሉም ክልል መንግሥታት ጽ/ቤት የመገንባት መብት አላቸው።ለሁሉም ዘላቂ ሰላምና አንድነት እንዲሁም እድገት የሚበጀው ግን የክልል አወቃቀርና የጎሳ ፖለቲካ ሲወገድና ፍጹም ዴሞክራሲያዊና ኢትዮጵያዊ የሆነ ሥርዓትና ፍትሕ ሲሰፍን ብቻ ነው። የጎሰኞቹ ፌዴራሊዝም ለኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም የሚረባረቡበትና የተሳሰሩበት የቃል ኪዳን ውል ሳይሆን የሌቦችና የአገር አፍራሾች ጥምረት መሆኑን ባለፉት ዓመታት የተፈጸመው ከሚበቃ በላይ ማስረጃ ነው።

በለገሃር ባቡር ጣቢያ፣ ጥንታዊና ታሪካዊ ቦታ የቅርስ ቤቶች ፈርሰው ለአንድ ያረብ ባለጸጋ መሸጡ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።አብይ አህመድ እዬሾፈረ እንደ በግ ሙከት አስመርጦ በሸጠው የከተማው መሃል ቦታ ከሚሠራው ሕንጻ በወቅቱ በቦታው ለነበሩት ሰዎች መኖሪያ ቤት እንደሚሰጣቸው ተገልጾ ነበር፤አሁን ላይ ግን አንድ መኝታ ቤት ያለው በ150 ሺህ ዶላር ማለትም 8 ሚሊዮን 250 ሺህ ብር በላይ የከፈለ ሊገዛ እንደሚችል ተገልጿል።ከድሃው እዬቀሙ ቺብችቦ መክበር የኦሕዴድ መተዳደሪያ

ደንብ ነው ስንል ይህንን አይነቱን የዘረፋ ተግባር ዋቢ በማድረግ ነው።አገር የመላው ሕዝብ ይዞታ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።ጥቂቶች ወይም አንድ ግለሰብ የሚያዝበት የግል ንብረት አይደለም።በአገር ውስጥ ባለ ማንኛውም የተፈጥሮ ጸጋና ሃብት ባለቤቱ ሕዝብ ነው።ባለፉት ስርዓቶች ግን ያገሪቱ ንብረትና የተፈጥሮ ሃብት ብቻ ሳይሆን በዜጎች ህይወትም ላይ የሚፈርዱትና የሚወስኑት በጉልበትና በሴራ ሥልጣኑን የተቆጣጠሩት ጥቂት አምባገነኖች ናቸው።የአሁኑ ግን ከሁሉም ጊዜ ይብሳል።

ሌላው የሰሞኑ አሳሳቢ ጉዳይ የትግራይ ሕዝብ ከመቀሌና አድዋ እዬፈለሰ በብዛት ወደ አማራው ክልል መግባቱ ነው።ወያኔ የጥቃት ክንዱን ለማሳረፍ ባቀደባቸው በቆቦና አላማጣ እንዲሁም ሌሎች ከተሞች በስደት የመምጣቱ ጉዳይ ከጀርባው ያዘለው ምስጢር ካለ በቅጡ መመርመር ያሻል።እርግጥ ነው የተቸገረና ወንጀል ያልፈጸመ ንጹሕ ሕዝብ ለምን መጣህ ወግድ አይባልም፤ተቀብሎ ማስተናገድ የኢትዮጵያውያን በተለይም የአማራው ማህበረሰብ ባሕልና ልማዱ ነው።የትግራይ ሕዝብ ቢያውቅበት ኖሮ ከሌላው ወገኑ በተለይም በብዙ የታሪክ፣የባሕል፣የእምነትና ማህበራዊ ትስስር ካለው ከአማራው ሕዝብ የቀረበ ወዳጅና አጋር የለውም። የወያኔን ድርጊትና ወንጀል ተቃውሞ የመጣ፣ለችግር የተጋለጠ ሴትና ሕጻናት፣አሮጊትና ሽማግሌ ቀርቶ ወጣትም ቢሆን በር ሊዘጋበት አይገባም።መጠንቀቅ የሚያስፈልገው ወያኔ ከሚያካሂደው የወረራ ስልት ጋር የተቆራኘ የጥቃትና የቅድመ ሠፈራ ዝግጅት አካል አለመሆኑን ማረጋገጥ ነው።እስከአሁን ድረስ በሦስት ቀናት ውስጥ ከ60ሽህ በላይ ሰዎች የገቡ ሲሆን ቁጥሩ ይጨምራል ተብሎ ይጠበቃል። ወደ ኤርትራም የሚገባው ሕዝብ ቁጥር ቀላል አይደለም።በትግራይ ያሉትም ተቃዋሚ ነን የሚሉ ቡድኖች በወያኔ ላይ የሚያሰሙት ተቃውሞ መጨመሩ ተሰምቷል። ወያኔ ቢወድቅ የሌሎቹ መምጣት ለኢትዮጵያ አንድነትና ሰላም የሚረዳ ይሁን አይሁን ወደፊት የሚታይ ይሆናል። እንደያዙት አቋም ከሆነና ከስህተታቸው ካልተማሩ እነሱም ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ትግራዊነትን እንደሚያስተናግዱና በዚያ አቋማቸው ከወያኔ እንደማይለዩ ነው። በሌላውም አቅጣጫ ከወሎጋ ወደ አማራው ክልል የሚገቡ ሰዎች ቁጥራቸው በመጨመር ላይ ነው።ልዩ የሚያደርገው የኢትዮጵያን ነባር ሰንደቅ አላማ ይዘው ኦነግ የሚቆጣጠረውን መሬት አልፈው መምጣታቸው ነው። አመጣጣቸው የኦነግን የወደፊት ዓላማ ለማስፈጸም ከወያኔዎቹ ጋር በመናበብ የተደረገ አሻጥር ሊሆን የሚችልበት ዕድሉ ከፍተኛ ስለሆነ እነዚህንም በዓይነቁራኛ መከታተል ተገቢ ነው።

ወደ ኦሕዴድ መራሹ የብልጽግና ጠቅላላ ጉባኤ ስናመራ ለመታዘብ ከውጭ አገር የያገሩ ተወካዮችና ምሁራን ከሓሙስ ጀምሮ ገብተዋል።የፓርቲው ስብሰባ ዝግጅት የአባ ቢያ አብይ አህመድን የንግሥና ክብረበዓል አስመስሎታል።በመክፈቻው ላይ አብይ አህመድ ባደረገው ንግግር ስለዝግጅቱና አዳራሹ እንዲህ ብሏል። ይህንን የመሰለ ውብ የስብሰባ አዳራሽ ለተመለከተ እውነት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ወይስ ቻይና ሳይል አይቀርም።አዎ የቦታው ማሸብረቅ፣የታዳሚው መሽቀርቀር፣የድግሡ መጠን ሲታይ እርሃብ፣ጦርነት፣መፈናቀል፣የኑሮ ውድነት የሚያምሰው ሕዝብ፣በማንነቱ የሚጨፈጨፍበት፣መጠነ ብዙ ችግር የሰፈነበት፣ለመኖርና ላለመኖሩ ፈተና ውስጥ ያለ አገር አይመስልም።ይሉኝታ ቢስ፣ከራሳቸው ደስታና ምቾት ባሻገር የማያስቡ ጅቦች፣በሥልጣን የባለጉበትን ጣራ የሚያሳይ ዝግጅት ነው።

ውሸትና መቀደድ የማይታክተው አብይ አህመድ ስለፓርቲው ሲናገር ብልጽግና በፈጣሪ ፈቃድ የተወለደ፣እስካሁን ድረስ ካሉትና ከነበሩት ሁሉ የላቀ ዓላማና ግብ፣ጥራትና ብቃት፣ብዙ ደጋፊና አባላት ያሉት፣በመጤ ህሳቤ ሳይሆን በአገር በቀል የመደመር ሃሳብ እራሱን የገነባ፣በኢትዮጵያዊነት መንፈስ የተተከለ፣እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ፓርቲ፣የተለያዩ ፓርቲዎች የተሰባሰቡበት፣ተፎካካሪ ፓርቲዎችን በሥልጣን ቦታ ላይ ያካተተ፣የእራስን ዕድል በራስ የመወሰንን መብት በተግባር የገለጸ፣ ችግርን በጉልበት ሳይሆን በብልሃት የሚፈታ፣ትናንትና ከነበርንበት ጦርነት አውጥቶ ዛሬ ለሰላምና

ለብልጽግና እንድንቆም ያደረገ ፓርቲ ነው።ስለሆነም ተቃዋሚ ነን ባዮች ሳይቀሩ ሁሉም ዓለም በእኛ ላይ እምነትና ተስፋ ስላላቸው በጉጉት እዬጠበቁና እዬተከታተሉን ነው።ይህንን ሁሉ የውሸት ዝግንትል በሚከተሉት ምዕራፎች እንፈትሸው።

ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ በሚለው ላይ ይሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ የሚለውንም ጣል አድርገንበት ከስብሰባው ምን ሊገኝ እንደሚችል የሰሞኑን የውስጥ ግብግብ ዋቢ አድርገን ፣የአብይን ይቀጠቀጣል፣ ይጰዳል፣ግልጽ ጦርነት እንከፍታለን በሚለው ዛቻ ላይ የአዳነች አቤቤን እግሩ ይቆረጣል የሚለውን ፉከራ ስንጨምርበት፣በመካሄድ ላይ ያለውን አፈናና ማሳደድ ባናቱ ላይ ጠብ ስናደርግበት፣ የብልጽግና የወደፊት ጉዞ ፍንትው ብሎ ይታዬናል።የለዬለት አምባገነናዊ ጎሰኝነት በተለይም የኦሮሙማው ቡድን ይሉኝታ ቢስ ባህሪው ጎልቶ የሚወጣበትና የሚጠናከርበት ይሆናል።የተሰባሰቡት ይበልጥ የሚቀራረቡበት ሳይሆን ለመለያዬት ፊርማ የሚቀዱበት ሊሆን እንደሚችል የሚነፍሰው አዬር ያስተጋባል።ወላዋይ የተባሉትም የሚመነጠሩበት ጉባኤ እንደሚሆን ከጉባኤው በፊት የሚወረወሩት ዛቻዎች ያመላክታሉ። በስብሰባው ላይ ተአምር ካልወረደና ኢትዮጵያዊነት ፈንቅሎ ካልወጣ የስብሰባው ውጤት አገርን እንደ አገር የማስቀጥል ሳይሆን ውድቀቷ የሚፋጥንበትን ጎዳና ቀይሶ የሚለያይበት ሆኖ ይታዬናል።ይህንን አባባላችንን ለማጠናከር ወደ ዝርዝር ትንተናው ሳንገባ ብልጽግናን በሚቀጥሉት ጥያቄዎች ብቻ እንፈትሸው።

እውነት ብልጽግና ለኢትዮጵያ አንድነትና እድገት የቆመ ነው? ከወያኔ ኢሕአዴግ በስም ካልሆነ በምን ይለያል?አብይ አህመድስ እኛ የወያኔ ግርፍና ምልምሎች ነን ሲል ምን ማለቱ ነው? አንድ አካል አንድ አምሳሎች ነን ማለቱ አይደለምን? የነማን ስብስብ ነው?አገር ለማፍረስ በጎሳ ፌዴራሊዝም ስም የተዋቀረ አይደለምን?ክልል፣ብሔርና ብሔረሰብ የሚል ትርክት የተሸከመው ማነው?የአገርን አንድነት የሚያናጋ ሕገ-መንግሥት መመሪያው ያደረገው ማነው? እውነት ብልጽግና ሕዝብን በማንነቱ ወይም በሚከተለው ሃይማኖት የተነሳ ከማሳደድና ከመግደል፣ከመዝረፍና ከማፈናቀል የጸዳ ድርጅት ነው?ማነው አሳሪው፣ማን ነው አፈናቃዩ፣ማነው ከወያኔ ጋር ተደራድሮ አማራውን በማሳደድ መሬቱን አሳልፎ የሰጠበት?ማነው የኢትዮጵያን ድንበር አስደፍሮ አያገባኝም ብሎ የተቀመጠው? ማነው የአገሪቱን ሃብት የሚመዘብረውና ባላስፈላጊ የቅብጠት ወጭዎች የሚያባክነው?ማነው የአዲስ አበባን ነዋሪ ሕዝብ ከመኖሪያ ቤቱ እያባረረ ለጎሳ አጋሮቹ የሚያድለው?ማነው የኢንተራሃምዌን ስነልቦና እዬቀሰቀሰ ለባሰ ሕዝባዊ ፍጅት ዱላና ቆንጨራ የሚያቀብለው? እውነት ኢትዮጵያ ከጦርነት አውድ ወጥታለች ?ወጣቱን ሰድበኸኛል እያሉ ማሳደድ ፣ማሰርና ማሰቃዬት፣ ችግርን በብልሃት እንጂ በጉልበት አንፈታም የተባለውን የአብይን ቀደዳ እውነትነቱን ያሳያል? መፍትሔ ካላበጀንለት ዛሬም እንደ ትናንትናው፣ነገም እንደዛሬው የግፍ ቀንበር ተሸክሞ መዝለቃችን አይቀሬ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከብልጽግና ተብዬው ስብስብ የተሻለ ስርዓትና ፍትህ አገኛለሁ ብሎ የሚጠብቅ ከሆነ የአህያ ብልት ይወድቅልኛል ብሎ ሲከተል የነጋበትን ጅብ መሆን ነው።የሚያዋጣው እራሱን ለሕዝባዊ አመጽ አዘጋጅቶ መፋለምና ያገሩና የራሱን እጣ ፈንታ ወሳኝ መሆን ነው።መታለልና መዘናጋት፣መለያዬትና እርስ በርስ መናቆር ይበቃል እንላለን።ሕዝባዊ ኮሚቴ ፈጥሮ እዬተናበበ ትግሉን ያፋፍም እንላለን።እንደ የካቲቱ ወይም እንደ ሱዳኖች ወይም እንደ ሰማንያዎቹ መጨረሻ እንደ ፖላንዶች ሕዝባዊ ንቅናቄ የትብብር መድረክ (ሶሊዳሪቲ ፎረም) መስርቶ ከመታገል ውጭ መፍትሔ የለም።እኛም የትብብር መድረኩ አባል ለመሆን ዝግጁዎች ነን።

ሕዝባዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ይመሥረት!ለሕዝባዊ እምቢ ባይነት እንዘጋጅ!!በሕብረት ጎሰኝነትን ገለን እንቅበር!!!